# ትናንትና ማታ በእልሜ

ከየትናየት አገር

በእውን ቤቴ ሆኜ በእልሜ ባህር ማዶ፣
ቦታው ለምለም ሳለ፣ ቀዝቃዛ በረዶ፣
በዕጹብ ድንቅ ሕንፃዎች፣ ሰፋፊ መንገዶች፣
በጋ ልምላሜን በተካኑ ዛፎች፣
በፈኩ ባማሩ ፍንጥቅጥቅ አበቦች፣
ያጌጠች ከተማ ደርሼ ይመስለኛል፣
ሽምግልና ይዘው ሰዎች ይታዩኛል።

የአገር ባዳ ዕንግዳ መሆን ቢሰማኝም፣
የወገኔ ቀለም ከሩቅ አልጠፋኝም።
ሳይ፣ ሁሉም ተሰባስበው፣
ባሳብ ተደጋግፈው፣
ሰላምን ግን አድርገው፣
ድልድይ ማለፊያውን፣
መሸጋገሪያውን፣
ምክክር ጀምረው፣
በእማማ ህመም ላይ በጥብቅ ይዘክራሉ፤
ይህ ይሁን፣ ያ ይሁን መላ ይመታሉ።

ታዲያ ይመስለኛል፣

የእኔም ጭንቀቴ

እመም ራስ ምታቴ፣

መጋኛ ዉጋቴ፣

ይኸው ነበርና፣ አሁንም ነውና፣

ያስፈልጋል መስማት ብዬ በጥሞና፣

በተስፋ ሽብረክ አልሁ፣

ምኞታችሁ እልሜ፣ ቃላችሁ ቃሌ አልሁ።

ከዚያም ይመስለኛል፣

የግልግል መምጫን ከአድማስ ጫፍ እያየሁ፣

በተመስጦ ሆኜ  እ ህ ህ ስል እያለሁ፣

ወደያው ከመቅጽበት ሃሳብ ደፈረሰ፤

ሥጋት ጥርጣሬ ጭራሽ ተባባሰ።

ሰውም ተደናቅጦ ምንድን ነው? ምንድን ነው? ሲባባል፣

ለካስ ዕባብ በዕባብ አካባቢው ኖሯል!!

ይህንን አልሜ ብንን ስል ድንገት፣

ቀፈፈኝ ጠላሁት የዕባብን ትምሳሌት።